የገለፃና የምልልስ ፋይዳ በአደፍርስ የመጀመሪያ ምዕራፍ[1]

ፈቃደ አዘዘ

1. መግቢያ

ዳኛቸው ወርቁ የካቲት 16/1928÷ ተወልዶ÷ በቅርቡ÷ ኅዳር 22/1987 ከመካከላችን በሞት የተለየ ደራሲና ምሁር ነው። በአማርኛና በእንግሊዝኛ ልዩ ልዩ የፈጠራ ድርሰቶችንና ፅሁፎችን የፃፈ በመሆኑ÷ በተለይ ደግሞ በዩኒቨርሲቲ መምህርነቱ÷ አደፍርስ በተባለው የአማርኛ ልቦለዱ÷ *The Thirteenth Sun* በተባለው የእንግሊዝኛ ልቦለዱ እና እምቧ በሉ ሰዎች በተባለው የግጥም መድበሉ ይታወቃል። ከነዚህ በተጨማሪ የፅሁፍ ጥበብ መመሪያ በተባለው መፅሃፉና ከአምሳሉ አክሊሉ ጋር ባዘጋጀው የአማርኛ ፈሊጦችም በተማሪዎችና በስነፅሁፍ ተመራማሪዎች ዘንድ የታወቀ ነው። በኢትዮጵያ የስነፅሁፍ ታሪክ ውስጥ ያለውና ወደፊትም የሚኖረው ቦታ በጥልቅ ምርምር የሚወሰን ቢሆንም ከወዲሁ ልንሰነዝረው የምንችለው አጠቃላይ አስተውሎት አለ። እስከዛሬ የታተሙትን የአማርኛ ልቦለዶች በቅርብ ስንመረምር የምናስተውለው ዓቢይ ነጥብ ÷ አደፍርስ÷ በተለይ በአፃፃፍ ቴክኒኩ÷ እመርታ የታየበት ልቦለድ መሆኑን ነው። በዚህ መጣጥፍ ውስጥ የዳኛቸው ወርቁን ሥራዎች በሙሉ ገምግሞ በድርሰቶቹ ውስጥ የሚገኙትን ረቂቅ ቴክኒኮች ማሳየት አይቻልም። ይህንን በሶስት አራት ዓመት ውስጥ ለማድረግ የሚችለው የደራሲውን ስራዎች ይዞ÷ አንድ ጥሩ መፅሃፍ ለመፃፍ÷ ዕውቀቱና ጊዜው ያለው ምሁር÷ ወይም የዶክትርና ጥናት የሚያደርግ በሳል የስነፅሁፍና የማኅበረሰብ ዕውቀት ያለው ተመራማሪ ነው። ይህ ማለት ግን÷ ከፍ ብለን የጠቀስነው ዓይነት ጥናት ተደርጎ ለስነፅሁፍ ባለሙያዎችና ዘለቅ ያለ የስነፅሁፍ ዕውቀት ላላቸው ሌሎች አንባቢዎች እስኪቀርብ ድረስ እጃችንን አጣጥፈን መቀመጥ አለብን ማለት አይደለም። ሌላው ቢቀይ÷ በተለይ አደፍርስን በሚመለከት ተደጋግሞ የሚነገረውን የአፃፃፍ ቴክኒክ ለማሳየት መሞከር ያስፈልጋል። የዚህ መጣጥፍ ዓላማም ዳኛቸው ለአማርኛ ልቦለድ ያስተዋወቀው የአፃፃፍ ቴክኒክ የታመቀበትን የመጀመሪያ ምዕራፍ ብቻ ወስዶ በገለፃ (description) እና በምልልስ (dialogue) አማካይነት ያበረከተውን አስተዋፅኦ በተለይ ለስነፅሁፍ

ተመራማሪዎች በማመልከት አካዳሚያዊ ውይይት መክፈት ነው፡፡ መጣጥፉ ከዚህ 'መግቢያ' ሌላ ሁለት ክፍሎች አሉት፡፡ በመጀመሪያው ክፍል በዳኛቸው አደፍርስ ላይ እተፃፉት ፅሁፎች ላይ ሂሳዊ ክለሳ (critical review) ይደረጋል፡፡ እንደሚታወቀው÷ የዚህ አስፈላጊነት የመጣጥፉ ርዕስ ጉዳይ በሆነው ነጥብ ላይ የተባሉ ነገሮች መኖር አለመኖራቸውን ለመመርመርና÷ በደራሲው ሥራዎች ላይ ምርምር ለማድረግ የሚያስቡ ቢኖሩ እነርሱን ከምንጮቹ ጋር በጥቅሉ ለማስተዋወቅ ነው፡፡ በሁለተኛው ክፍል የአደፍርስ የመጀመሪያው ምዕራፍ ይተነተናል፡፡

በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ከልቦለዱ ብዙ ጥቅሶች አልተጠቀሱም፡፡ ይህ የተደረገው መጣጥፉን ከሚገባው በላይ ላለማስረዘም ሲባልና፤ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ዓላማው አካዳሚያዊ ስለሆነ÷ በመስኩ ያሉ ባለሙያዎች ልቦለዱን ይዘው ትንተናውን ይከታተላሉ፤ ይመረምራሉ÷ ይከራከራሉ ተብሎ ስለታመነ ነው፡፡

2. በዳኛቸው አደፍርስ ላይ የተፃፉ ፅሁፎች አጭር ሂሳዊ ክለሳ

አደፍርስ ላይ የተፃፉትን ፅሁፎች በሁለት መወገን ይቻላል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ልቦለዱን ከሌሎች የአማርኛ ልቦለዶች ጋር እንደሚያነፃፅሩ በርእሶቻቸው ገልፀው የሚነሱ ሲሆኑ÷ ሁለተኛዎቹ ደግሞ ልቦለዱን ለብቻው መርጠው በውስጡ ስላሉ ልዩ ልዩ ጉዳዮች የሚፅፉ ናቸው፡፡ እነዚህን በዝርዝር መተንተን እራሱን የቻለ ዓቢይ ሥራ ነው፡፡ ስለዚህ ስራዎቹን ባጭር አስተዋውቀን ከዚህ መጣጥፍ ርዕስ ጋር በቀጥታ በሚገናኝ መንገድ ያነሷቸው ነጥቦች ሲኖሩ እነርሱን አሳጥረን እናቀርባለን፡፡

2.1. አደፍርስን ከሌሎች ልቦለዶች ጋር በደባልነት የሚያነሱ ፅሁፎች

በዚህ ክፍል ውስጥ የምናነሳቸው ሥራዎች የዲግሪ ማሟያ ፅሁፎች[2] (ካሁን በሁዋላ ዲማፅ) እና በጋዜጣ ላይ የወጡ መጣጥፎች ናቸው፡፡ ከቢ.ኤ. ዲማፆች መሀል አምስቱ በየርእሶቻቸው የጠቆሟቸውን ይዘት-ነክ ጉዳዮች የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ተንሳይ ይገዙ (1978) "ፊውዳል ወይዛዝርት"ን፤ መስፍን አባተ (1978) "ማህበራዊ ልማድ"ን፤ ሞሴ ፈንታ (1978) "ሃይማኖት"ን፤ ታጠቅ ታደለ (1981) "ቅናት"ን፤ ይልማ ደምሰው (1986) "ማህበራዊ ዕይታ"ን መሠረት አድርገው ስለ አደፍርስና እያንዳንዶቻቸው ስለመረጧቸው ልቦለዶች ፅፈዋል፡፡ ሌሎች አምስት ዲማፆች

ርፅን የሚመለከቱ ናቸው:: ሽባባው ወሌ (1976)፥ በአደፍርስና፡ በ ባሻገር ውስጥ ስላለው የገፀባህርይ ግጭትና ጭብጥ ፅፏል:: መሀመድ 8) ስለግንት ሲፅፍ ጥቂት መስመሮችን ከአደፍርስ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሶ ደራሲው ገለፃውን በሰውኛ ዘይቤ አግንኖ ማቅረቡን ብቻ ይናገራል:: ዲ(1978) በአምስት ልቦለዶች ውስጥ ስላሉ ገለፃዎች (descriptions) ፍ በርእሱ የተነገረ ቢሆንም፥ በፅሁፉ ውስጥ ያነሳቻቸው ልቦለዶች ቁጥር በላይ ነው:: ስለዚህም በአንድ ሙሉ ልቦለድ ላይ እንኳን በቀላሉ አዳጋች የሆነውን የገለፃን ጉዳይ፥ ከስምንትና ከዘጠኝ ልቦለዶች ጥቅሶች እየወሰዱ ለመፃፍ መሞከር፥ ድፍረት የተሞላባቸውን ጥቅል ከማኸጎድጎድ ሊያልፍ አልቻለም:: የሥነቃል አጠቃቀምን ተው የትንሳኤ ብርሃኔ (1978) ዲግፅ በአደፍርስ የመጀመሪያ ምዕራፍ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ያወሳል:: አነጋገሮቹ ለልቦለዱ አፃፃፍ ያላቸውን ቴክኒካዊ ፋይዳ ከማሳየት ይልቅ ፍቻቸውን እመስጠቱ ላይ ያተኩራል:: ከዚህ ቀደም ፈቃደ (1973) ስለነዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ያስተዋለውን፥ አንዴ በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ እያስገባ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ የሃሳቡን ብኩርና ሳይናገር ይደጋግማል (1978፡ 1-4 ተመልከት):: "ማጠቃለያ"ውም ቢሆን በዚሁ በፈቃደ ፅሁፍ ውስጥ የተጠቀሱት የትውፊት ፋይዳዎች የሚያመለክቷቸውን የሃሳብ ማጠንጠኛዎች ("ለይዘቱ ማበልፀጊያ ፥ ለገፀባህርያቱ መቅረጫ፥ ለመቼት ገለፃ፥ ለአደራረስ ቴክኒክ ማጎልበቻ ወዘተ." የሚሉትን [ገፅ 93 ተመልከት] ሲደግም ነው የሚታየው):: ስለ ልብ ሰቀላ (suspense) የተፃፈው የቴዎድሮስ ካብታሙ (1981) ዲግፅ እና ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ዲግሪዎች በዚህ መጣጥፍ ውስጥ ስላጠናነው ምዕራፍ እና ስለ ርዕሰ ጥናቱ ያተኮሩበት ነጥብ የለም::

የአሰፋ አረጋኸኝ የኤ.ም.ኤ ዲግፅ (እ.ኤ.አ. 1981) ለአደፍርስ አንድ ምዕራፍ ሰጥቷል:: የልቦለዱ አፃፃፍ አዲስ መሆኑን ከማስታወቅና በዚህ አዲስነቱ ከሌሎቹ የአማርኛ ልቦለዶች መላቁን ከመንገር በቀር የ"አዲስነቱ"ን ልሂቅና ተንትኖ አሳይቷል ማለት አይቻልም:: ስለ ድምፀቀድ ቃላት (onomatopoeic words) አጠቃቀም ግን አንዳንድ መልካም ነጥቦችን ያነሳል፤ ስለቋንቋው ከባድነትም በጥቅሉ ይናገራል (ገፅ 37-42 ተመልከት)::

ቶማስ ኬን (እ.ኤ.አ. 1975)፥ ሬይዱልፍ ሞልቬር (እ.ኤ.አ. 1980)፥ ፍቅሬ ቶሎሳ (እ.ኤ.አ. 1983) በሥራዎቻቸው ውስጥ የዚህ መጣጥፍ ርእስ ነገር በሆነው የአደፍርስ የመጀመሪያ ምዕራፍ ያነሱት ነጥብ የለም:: ሳህለ ስላሴ ብርሃነ ማርያም የመጀመሪያውን ምዕራፍ "The most fascinating chapter in the entire book" (in Fekade (Comp.), 1992:313) በሚል ያደንቀዋል እንጂ ለመደመሙ ምክንያት የሆኑትን ነጥቦች አይጠቅሳቸውም:: ብርሃኑ ዘሪሁን (1962)' በፃፈው አጭር አቃቂር የልቦለዱን አዲስ አፃፃፍ በጥቅሉ በማድነቅና ለአንባብያን ሊከብድ መቻሉን በመግለፅ ላይ ያተኩራል:: በመጀመሪያው ምዕራፍ የመጀመሪያ አንቀፅ ውስጥ

ያጋጠመውን ሲገልፅም "ከታሪኩ ጋር ግንኙነት የሌላቸው የሚመስሉ የተንጠባጠቡ ቃላት፣ ማሠሪያ ግሥ የሌላቸው ዓረፍተ ነገሮች፣ የተገለበጡ ሐረጎች . . ." እያለ ነው:: ልቦለዱን አዲስ ከሚያደርጉት ጉዳዮች መሀል አንዳንዶቹን በዚህ መልክ መግለፁ ይመስላል::

በዚህ ንዑስ ክፍል ውስጥ የምናነሳው ሌላ የኤም.ኤ. ዲግፅ በዳኛቸው ወርቁ ሥራዎች ላይ ተከሉ ሚናስ (እ.ኤ. አ 1983) የፃፈው ነው:: ተከሉ በአደፍርስ የመጀመሪያ አንቀፅ ውስጥ ካሉት ዝርዝሮች አንዳንዶቹን ይጠቅሳል:: ከውስጡ በከፊል ጠቅሶ ደራሲው አካባቢውንና ሰዎቹን በዝርዝር አስተውሎቱ መግለፁንም አስፍሯል (ገፅ 42):: በፅሁፉ ውስጥ ማስረጃ እየሰጠ ወይም እየጠቆመ ተንትኖ ባያሳይም በልቦለዱ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ገፆች ውስጥ ስለተሰጠው ገለፃ የሚጠቁመው ነጥብ አለ::

> *There is a sardonic touch of humour in this part of the novel which may be taken to be both the beginning and the end of the novel. It is from this part and around these words and phrases heaped up in the first two pages of the novel that the whole body of the novel unfolds. This is a part of the novel that calls for a close examination (45).*

ስለ አደፍርስ ተፅፈው ካገኘኋቸው ፅሁፎች መሠረታዊ የአፃፃፍ ስልትን የሚነካ ነጥብ በጥቅሉም ቢሆን የተጠቆመው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ጥቅስ ውስጥ ነው::[3] እርግጥ ከዚህ ሥራ በፊት ስለዚሁ ምዕራፍ፥ በ 1973 የሚቀጥለው ተፅፎ ነበር፣

> በልቦለዱ መጀመሪያ ላይ ባሉ ሁለት ገፆች ውስጥ በልዩ ልዩ ስልት የተሰደሩት ቃላትና ዐረፍተ ነገሮች የጠቅላላ ልቦለዱን ድባብ የሚያመለክቱ ናቸው:: አርማኒያ ". . . እግዜር ዓለምን ሠርቶ ሲያበቃ የተረፈውን ትርክምክም ያጎረበት እቃ ቤቱ . . ." (አደፍርስ፥ ገፅ 1) ያስመሰላት ምስቅልቅልነት - ዝርክርክነት - ዙሪያው - ጉድ - ግራነት. . . በወይዘሮ አሰጋሽ ሥጋ ለብሶ፥ እንደበት ገዝቶ ይመጣል:: . . . ድባቡ ጭፍግግ እንደመሆኑ የወ/ሮ አሰጋሽና የጭሰኛው ውይይትም - "ውይይት ነው" እንበልና- ልብ የሚጨፈግግ፥ ስሜት የሚያደነዝዝ ነው:: ... /ፈቃደ፥ 1985፥ ገፅ 13/[4]

ከዚህ በላይ ከፈቃደ መጣጥፍ የተወሰደው ጥቅስ፥ ስለ አደፍርስ የመጀመሪያ ምዕራፍ በሚፃፉ ፅሁፎች ውስጥ በጨረፍታም ሲጠቀስ አይታይም:: ይህ ፕሮብሌም ከብዙ የምርምርና የትምህርት ችግሮች ጋር የተያያዘ ስለሆነ በዚህ መጣጥፍ ውስጥ ልናተኩርበት አንችልም:: ስለዚህ ወደሚቀጥለው ንዑስ ክፍል እናመራለን::

2.2. አደፍርስን ብቻውን የተመለከቱ ዲግሪዎች

በዚህ ክፍል ከምንመለከታቸው ፅሁፎች የታሪክነህ አጥናፉ ዲግሪ (1970) ቀዳሚነት አለው:: ታሪክነህ፥ ስለዳኛቸው የአፃፃፍ ስልት (style) ጥናት ሲያደርግ በተለይ የቃላት አመራረጥንና የዐረፍተነገር አቀራረብን ሊመረምርሞክሯል:: ስለቃላት ሲፅፍ "ቃላተ ምሑር" በሚለው ንዑስ ክፍል ስድስት ግዕዝ ቀመስ ቃላት መርጦ ሥረ መሰረታቸውንና ፍቻቸውን ያስረዳል:: "ምስያ" (analogy) በሚለው ንዑስ ክፍል የአምስት ቃላትን አፈጣጠርና አዲስ አጠቃቀም ያወሳል:: ስለ ድምፀቀድ ቃላት እና ስለቀበሌኛ ቃላትም እንዲሁ ምሳሌዎች ይጠቅሳል:: ባጭሩ፥ በብድግብድግ (randomly) በተወሰዱ ምሳሌዎች ስለመረጣቸው ንዑሳን ርእሶች ያወሳል:: በልቦለዱ ውስጥ ስላለው የቃላት አጠቃቀም የሚናገረው ግን በጣም ቁንፅል ነው:: አንድ ጥሩ የዱክትርና ዲግሪ የሚያጽፈውን ጉዳይ ነው በ 13 ገፆች የዳበሰው:: ስለ ዓረፍተነገሮቹ መዋቅራዊ አቀነባበርም እንዲሁ አንዳንድ ምሳሌዎች ነው የሚጠቅሰ:: በተለይ ከዚህ መጣጥፍ ጋር የሚያያዘው ነጥብ ስለ ዓረፍተነገር ቅንብር ሲፅፍ፥ ከመጀመሪያው የልቦለዱ ምዕራፍ "ዝርዝራ" ለሚለው ንዑስ ክፍል የሚጠቅሰው ነው:: በዚህ መጣጥፍ፥ በምሳሌ 01፥ ውስጥ የተጠቀሱትን የእርሻ ቃላት ለብቻቸው አውጥቶ ጠቅሶ የገበሬውን ህይወት እንደሚያሳዩ ተናግሮ ያበቃል (ገፅ 25):: ከዚህ ሌላ፥ ስለ መጀመሪያው አንቀጽ ቴክኒካዊ ፋይዳዎች ያስተዋለው ነጥብ የለም:: ያም ሆኖ ግን፥ የታሪክነህ ሥራ መልካም ነጥቦችን የሚያነሳሳ፥ ከደህናዎቹ፥ ጥቂት ሥነፅሁፍ-ነክ የቢ.ኤ. ዲግሪዎች የሚመደብ መሆኑን አጠንክሮ ማስገንዘብ ይገባል::

የንብረት ምስክር (1971) ዲግሪ በቋንቋ ላይ ያተኩራል:: ስለ ቃላት፥ ስለ ዓረፍተነገሮችና ስለ አንቀጾች ቅንብር፥ ስለ ምሳሌያዊ አነጋገሮችና ዘይቤዎች ምሳሌዎችን እየጠቀሰ የሚዘረዝር ሥራ ነው:: ከርሱ ቀደም ብሎ ከተሰራው፥ ከታሪክነህ ዲግሪ ጋር መሠረታዊ ተመሳስሎ ቢኖረውም በዝርዝር ብዛት ይለያያሉ:: የታሪክነህን ሥራ ግን ንብረት ምስክር ጨርሶ አያነሳም:: ሥራዬ ብሎ ሁለቱን ዲግሪዎች ለማስተያየት ለሚሻ ተመራማሪ ግን ስለ ክፍላችን የቢ.ኤ. ዲግሪዎች የሚናገረው ይኖራል:: ባጭሩ ሥራው ነጋሪና ገላጭ እንጂ፥ የአፃፃፍ ስልትን እየተነተነ፥ የሚዘረዝራቸው ቋንቋ-ነክ ምሳሌዎች ያላቸውን ቴክኒካዊ ፋይዳ ተገንዝቦ ለማስገንዘብ የሚሞክር አይደለም::

የታምራት ተስፋዬ (1972) ዲግሪ፥ ስለዋናው ገፀ ባህርይ ስለ አደፍርስ የተፃፈ ሲሆን፣ የዘውዴ አክሊሉ (1973) ደግሞ በልቦለዱ ውስጥ ስላሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች የተፃፈ ነው:: ዘውዴ፥ የመሬት ከበርቴዎች "በምሳሌያዊ አነጋገሮች በመጠቀም ጭሰኞቻቸው ፈርተው እንዲገዙ ያደርጉ ነበር" (ገፅ 20) ብሎ፥ በአደፍርስ የመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ ከተጠቀሱት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ጥቂቶቹን ይጠቅሳል:: በእነርሱም አማካይነት የወ/ሮ አሰጋሽን ባህርይ ለመጠቆም ይሞክራል:: ከዚህ አልፎ የምሳሌያዊ አነጋገሮቹን ቴክኒካዊ ፋይዳ አይመረምርም::

ከዚህ በላይ ባጫጭሩ የከለስናቸው ጽሁፎች በአደፍርስ የመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ ያለውን፥ በተለይ የመቼትን ገለፃና የምልልስን ቴክኒካዊ ፋይዳ እንደማይመረምሩ አመልክተናል። ከዚህ ቀጥሎ በዚህ መጣጥፍ ውስጥ በመቼትና ምልልስ ላይ በማተኮር የመጀመሪያውን ምዕራፍ ለመተንተን እንሞክራለን።

ጥቅስ 01

ቁንዲ አንገቷን አስግጋ ቃፊርነት የቆመች መስላለች። የዓዋዲና የጅውሃ ጅረቶች ደረታቸውን ለፀሐይ ሰጥተው ይምቦገቦጋሉ። ሰማይና ምድር የተገናኘበት፥ ሕይወት ያሸለበችበት የሚመስለውን በስተግርጌ የሚታይ ሜዳ አባራ ረግቶበታል። በየስርጓጉጡ፥ በየሸለቆው፥ በየተረተሩ፥ በየሸንተረሩ - ጉርጅ፥ ወፍ ዋሻ፥ ዋንዛበረት፥ ጃናቦሬ፥ የልቶኪ፥ መጢ፥ ዲያውዲያምባ፥ ዓዋዲ፥ ጨኖ፥ አጋምበር፥ ዋይሎ፥ ደብረ ሲና፥ አርማኒያ፥ ሸረሸር፥ ወይን ውሃ፥ ማንያምባ፥ አብዲላቅ፥ ማፉድ፥ ግልዲማ፥ ካሴ አገር፥ ራሳ፥ መዘዞ፥ አያበር፥ ቀወት፥ ወጃ፥ ጠማሚት፥ ሾተል አምባ --- በየከፍተኛዎቹ ጉባዎች - ግፍት ሚካኤል፥ ጉርጅ ሚካኤል፥ ዋንዛበረት ሚካኤል፥ ዶቃቂት ሚካኤል፥ ሳራምባ ሚካኤል፥ ራምሴ ሚካኤል፥ ማኒያምባ ሚካኤል፥ የልቶኪ ሚካኤል፥ ዋይሎ ሚካኤል፥ ሐራምባ ሚካኤል፥ ማፉድ ሚካኤል፥ ወጃ ሚካኤል --- የይፋትና ጥሙጋ አውራጃን ጣርማበር ተራራ ላይ ሆኖ ሲመለከቱት፥ እግዚአብሔር ዓለምን ሰርቶ ሲያበቃ የተረፈውን ትርክምክም ያጎረበት እቃ ቤቱ ይመስላል።-ሸለቆው፥ ጉባው፥ ተራራው፥ ገመገሙ፥ ጭጋጉ፥ አባራው ሕይወትን አፍኗት ተኝታለች።-ያቺ በሌላው፥ አገር የምትጣደፈው፥ የምትፍለቀለቀው፥ የምትምቦለቦለው ሕይወት እዚህ እፎይ ብላለች - በርጋታ፥ በዝግታ፥ ታምማለች፤ በተገማሸረ መስክ ውስጥ እንደሚብሰከሰክ ውሃ --- ሰኞ፥ ማክሰኞ፥ ረቡዕ --- ልደታ - (ራጉኤል)- አባ ጉባ - በዓታ - ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ - አቡዬ ጻድቁ - የሱስ ክርስቶስ - ሥላሴ - አርባዕቱ እንስሳ - ቶማስ ሰማዕት - መስቀለ የሱስ - ቅድስት ሀና - ቅዱስ ሚካኤል - እግዚአብሔር አብ - (ሩፋኤል) - አቡነ አረጋዊ - (ገብረክርስቶስ) - ሕፃኑ ቂርቆስ - ኪዳነ ምሕረት - እስጢፋኖስ ቀዳሜ ሰማዕት - ኤዎስጣቴዎስ ጻድቅ - ገብርኤል - ሀንፀታ - ማርያም-ሐዋርያት - ጊዮርጊስ - ተክለ ሃይማኖት - መርቆሬዎስ - ዮሴፍ - መድኃኔ ዓለም - አማኑኤል - በዓለ እግዚእ - ቅዱስ ማርቆስ - ደመራ - መስቀል - ቅዱስ ዮሐንስ - ገና - ጥምቀት - ፋሲካ - ትፈስሳለች - ታምማለች፡ ሕይወት፥ በተገማሸረ መስክ ውስጥ እንደሚብሰከሰክ ውሃ --- ወገብ በመዛወር - በመናፈስ - በማሽራሸት - በመዋጥ - በማድቀቅ - በማኘክ

> በመጉረስ - በመጋገር - በማቡካት - በመከርተፍ፡ በመሰለቅ በመጎተር - በመጎድጎድ - በመጫን - በመውቃት - በመከመር፡ በማዉደ፡ በማረም - በመቆፈር - በመጎልጎል - በመትለም በማረስ በመጨፈቅ - በመጥረግ - ከብት በማሰማራት - የከብት ራት በማስገባት ማምሻ እንጨት በመልቀም÷ ታልፋለች÷ ትፈስሳለች፤ ታምማለች ሕይወት፥ በተገማሸረ መስክ ውስጥ እንደሚብሰከሰክ ውሃ። በፋሲካ በፍልሰታ - በገሐድ - በነነዌ - በሑዳዴ - በጾመ ሐዋርያት ባርብ ሮብ ትደለላለች÷ ትዳከማለች - በታናሽ (ሹልዳ) በታላቅ በጭቅና- (ሰብራዳ) - በሽንጥ - በፍርምባ - በማህል አገዳ (ጡንቻ) - በወርች (ነብሮ) - በጎድን ተዳቢት (ቤተ ሳልገኝ) - በምላስና ሰምበር - በልብ - በጉበት - በኩላሊት - በጨጓራ - በሽምፍላ - በቅንጣቢ - በነጭ ጤፍ - ጥቁር ጤፍ - ጥቁር ጤፍ - ነጭ ጤፍ - በማሽላ - ዘንጋዳ - ጨረቂት - በባቄላ - በሽምብራ - በቀይ ወጥ - በአልጫ - በአልጫ - በቀይ ወጥ - በጠጅ - በብርዝ - በጠላ - ቅራሪ፡ እንደገና ደግሞ ቲፍ ብላ ትሞላለች - ትፈስሳለች - ትፈስሳለች - ትፈስሳለች - ታምማለች፡ ሕይወት በተገማሸረ መስክ ውስጥ እንደሚብሰከሰክ ውሃ።- ኤዛና - ዐምደ ጽዮን - ዘርአ -ያዕቆብ - ሱስንዮስ - አምኀየስ - አብዬ - መሳፍንት - ዮሐንስ - ቴዎድሮስ - ምኒልክ - ደለሏን ትተዋለች - አዝብጤ - ጫልቱ - ለጼሳ - ጎንጤ - ሐዳስ - ቀመሩ - አዛለች - ወርዶፋ - አርያም - ጨቡዴ - አያንቱ - ገብሬ - ተዋበች - ነስሩ - መገርቱ - ቢራቱ - ለተሚካኤል - እርገጤ - አያንቱ - ሐጎስ - ኩሬ - ጉድባ - ጉድባ - ኩሬ - ክትር - ክትር - ጉድባ - ጉድጓድ - ኩሬ - ክትር - ጎለንታ - መስኖ - በርጋታ- በዝግታ - ትፈስሳለች - በሌላ አገር የምትጣደፈው - የምትፍለቀለቀው - የምትምቦለቦለው፡ ይችው ሕይወት . . . (አደፍርስ÷ 5-6)

ይህ ጥቅስ በልቦለዱ ውስጥ የሚተረከው ታሪክ የሚካሄድበትን አካባቢ ባልተለመደ ሥልት የሚስል ነው። በዚህ አካባቢ የሚንቀሳቀሱት እና የሚኖሩት ገፀባህርያት አንዳንድ ገፅታዎችም በዚሁ ገለፃ እና በሚከተሉት ምልልሶች ውስጥ ተጠቁመዋል። ባጭሩ የልቦለዱን ኀሊናዊና አካላዊ "አትሞስፌር" (atmosphere) በመጀመሪያዎቹ 16 ገፆች ለመሳል የተደረገው ሙከራ በዚህ ገለፃ የጀመረ ይመስላል። ይህ ማለት÷ አንባቢው በምናቡ÷ የአካባቢውን ጠረንና አየር ለማሽተት÷ ቀለምና ቅርፁን ለማየት÷ ድምፁን ለመስማት÷ አካሉን ለመዳሰስ÷ ቃናውን ለማጣጣም÷ እና ጠቅላላ ስሜቱንም ስሜቱ ለማድረግ እንዲችል ማድረግ ነው ማለት ይቻላል። ይህንን ዘርዘር አድርገን እንመልከት።

የ<u>አደፍርስ</u> አጀማመር ከብዙ "ታዋቂ" የአማርኛ ልቦለዶች÷ ማለትም÷ በአማርኛ ስነጽሁፍ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች ዘንድ ከሌሎቹ የአማርኛ ልቦለዶች ይበልጥ ስማቸው ተደጋግሞ ከሚነሳው÷ የተለየ ነው። ቁምነገሩ የመለየት ብቻም አይደለም። የልዩነቱ ምንጭ በአማርኛ ልቦለድ ውስጥ ያልተለመደ የገለፃ ቴክኒክ

በዚህኛው ውስጥ መታየቱ ነው:: እንደሚታወቀው፥ አንድ ገለፃ ግዑዝ (አካላዊ)፥ ስነልቡናዊ እና ባህላዊ መረጃ እና ስሜት ይይዛል - ያስተላልፋል:: ለምሳሌ አንድን ተራራ ለተራራነቱ ለታሪኩ ብቻ ሲባል መግለፅ ይቻላል:: ቁመቱን፥ ወርዱን፥ ስፋቱን እየጠቀሱ፥ በጦርነት ወቅት በላዩ ላይ የሞተውንና የቆሰለውን ሰው ብዛት እየደረደሩ ብቻ መግለፅ ይቻላል:: የተራራውን ግርማ ሞገስ፥ "ጥላቢስነት"፥ አስፈሪነት፥ አስደማሚነት፥ በላዩ የበቀሉትን ዕፀዋትና ዛፎች እየገለፁ መፃፍም ይቻላል:: ከሰዎች፥ ከእንስሳት፥ ከተክሎችና ከወንዞች የህይወት ትስስር ጋር በተጣጣመ/ባልተጣጣመ መልኩ የተራራውን ውበትም ይሁን ጥፉፍነት መግለፅ ይቻላል:: መንገዶቹ ብዙ ናቸው:: እዚህ ዘርዝረን የምንጨርሰው ትውራዊ ጉዳይ አይደለም:: ለጊዜው፥ ዋናው ቁምነገር፥ አንድ የአካባቢ ገለፃ የተገላጪውን ውስጣዊም ሆነ ውጭያዊ "ባህርይ" ለማሳየት የሚያገለግል ቴክኒክ መሆኑን መገንዘብ ነው:: የአገላለፅ ቴክኒኩ እንደየደራሲው ክሂልና አላማ፥ እንደሚገለፀውም ነገር ምንነት/ማንነት ይለያያል:: ስለዚህ "በዳኛቸው <u>አደፍርስ</u> የመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ ያለው ገለፃ ምንድነው? እንዴት ቀረበ? ዓላማው ምንድነው?" የሚሉትን ጥያቄዎች በጥቅሉ ለመመርመር እሞክራለሁ::

ገለፃውን ተከትለን፥ ተፈጥሮአዊ አካባቢውን በምናባችን ስንቃኝ በቀላሉ የሚታየን፥ በግልፅ የምንረዳው፥ ቀላል ምስል አይታየንም:: ባንድ በኩል እንዳስቸጋሪ እንቆቅልሽ ሊታይ የሚችል አካላዊ ገፅታ ነው:: አቶ ብርሀኑ ዘሪሁንንም ያወከው ይሄው ሳይሆን አይቀርም:: ስርጓጉጡ ... ሸለቆው ... ሸንተረሩ ... ጉባው ... ተራራው...ገመገሙ... ኩሬው ... ጉድባው... ክትሩ ... ጉድጓዱ ... ጎለንታው ... መስኖው ... የየዓይነቱ መልክዐምድር ስብስብ ነው:: ደራሲው፥ "እግዜር ዓለምን ሠርቶ ሲያበቃ የተረፈውን ትርክምክም ያጎረበት ዕቃ ቤቱ ይመስላል" ያለው፥ ሁኔታውን በውብ ምሳሌ ይገልፀዋል ማለት ይቻላል:: (በተለይ አካባቢውን ለሚያውቅ ሰው ገለፃው ትክክለኛ [Realistic] የሚባል ዓይነት ነው::) በመጀመሪያ፥ ደራሲው፥ አካባቢውን የሚቃኘው ከቁንዲ ግምባር (point of view) ይመስላል:: ቁንዲ "አንገቷን አስግጋ" እንደቃፊር የምትቃኘውን ዙሪያ ገባ የሚስልልን ይመስላል:: በኋላ ግን "ጣርማበር ተራራ ላይ ሆኖ" የሚመለከተው መሆኑን እንገነዘባለን:: የትም ሆነው ተመለከቱት አካባቢው ያው ትርክምክም ... ቁርጥርጥ ... ስብርብር ... ወጣ ገባ ... ነው.: ስሜትን ሊያስፈነድቅ የሚችል ውበት ብቻ ሳይሆን የተመልካቹን መንፈስ የሚጫጫነውም ግዙፍ ኃይል በገለፃው ውስጥ አለ ማለት ይቻላል:: ለዚህም ይሆናል፥ ውበቱን ከመቅፅበት ዘንግተን "በዚህ ውጥንቅጥ ውስጥ ያሉ ሰዎች እንዴት ይኖሩ ይሆን? በዚህ ጠባብ መሬትስ ምን ያደርጉበት ይሆን?" በሚሉ ጥያቄዎች የምንመታው:: ወዲያው ደግሞ "እግዜሩ ዓለሙን፥ ቆንጆ ቆንጆውን፥ ውብ ውቡን ሌላ ቦታ ሠርቶ፥ መልካሙን የፍጥረት ሥራ እሌላ አካባቢ አከናውኖ፥ ትርፍራፊውን ያጎረበት ነው ማለቱ የነዋሪዎቹን አበሳ እንድናስላስል ይሆን?" ማለታችን አይቀርም:: እንዲህ እንዲህ እያለ፥ በመጨረሻ

እውስጣችን የሚቀረው ግን አሳሳቢውና አስጨናቂው ዝባዝንኬ-ተራ (junk-yard) ነው። ተፈጥሮአዊ አካባቢው ለአቀማመጡ ሥርዓት የሌለው የቁርጥራጭና የጉማጅ ስብስብ ሆኖ ተገልጿል ማለት እንችላለን።

በሌላው ጠገግ፥ ይኸው አካባቢ አጥባቂ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች የሚኖሩበት መሆኑ ትእምርታዊ በሆነ መንገድ ተጠቁሟል። ከፍታዎቹና ጉባዎቹ በማያወላውል የበላይነት በሚካኤል ተይዘዋል። ይህም፥ ባንድ በተወሰነ አካባቢ ብቻ፥ በዚያ ላይ ደግሞ ባንድ ታቦት ስም ብቻ፥ የሚገኙትን ቤተ ክርስቲያኖች ብዛት በመዘርዘር፥ ቴክኒካዊ በሆነ ዘዴ የሀይማኖትን መንሰራፋት ያውጃል። ዝርዝሩን ደራሲው ገትቶት ነው እንጂ አላለቀም። በየወሩ የሚመላለሱት የየዕለቱ በዓላት ከነጣምራዎቻቸው ተደርድረዋል። የተጠቀሱት የዓመት በዓላትም የኦርቶዶክስ ክርስትና ተከታዮች በዓላት ናቸው። የሚጾሟቸውን ጾሞች በመደርደርም የአካባቢውን ሰዎች ማንነት ለመጠቆም ተሞክሯል።

አካባቢው፥ ከኤዛና እስከ ምኒልክ የሚወርድ የረዥም ዘመን ታሪክ እንዳለው ለመጠቆምም ጥቂት የነገሥታት ስሞችን በመዘርዘር ተጠቅሟል። እርግጥ ደራሲው የሚኖርበትን ዘመን ሳይጠቅስ በምኒልክ ነው የሚያቆመው። ይህንን ያደረገውም ያለበቂ ምክንያት አይመስልም። ባንድ በኩል፥ ወደፊት በልቦለዱ ውስጥ የሚሳለው ገጠራዊ ህይወት፥ በሌላ በኩል ደግሞ፥ ትእምርታዊ በሆነ መንገድ፥ በጠቅላላ የሀገሪቱ የገጠር የህይወት ስሪት ያለበትን ደረጃ እና ዘመን ማመልከቱ ይመስላል። ይህንን አስተውሎት፥ ወደፊት፥ የልቦለዱን መሰረታዊ ፍልስፍና (Weltanchung) ተገን አድርጎ፥ በዝርዝር መተንተን ያስፈልጋል። እስካሁን፥ ደራሲው፥ የአካባቢውን ተፈጥሮአዊ ገፅታ፥ የነዋሪውን ሃይማኖትና ታሪክ በመግለጽ በልቦለዱ ውስጥ የሚመጡት ድርጊቶች የሚከናወኑበትን ዐውድ መጠቆሙን ባጭሩ ተመልክተናል።

በዚሁ ገለፃ በአካባቢው የሚኖሩት ሰዎች ጎሳም በስማቸው አማካይነት ተጠቁሟል ማለት ይቻላል። በየስማቸው ብዛትም የሕዝብ ብዛታቸውን ተመጣጥኖ (proportion) ለመጠቆም ጥረት የተደረገ ይመስላል። (በጥቅሉ የማን ጎሳና የማን እንደሚመጣጠን ተጠቁሟል ማለታችን ነው እንጂ አኃዛዊ ቀመር በዚህ ገፅ ተስጥቷል ማለታችን እንዳልሆነ ግልፅ ነው።) የተጠቀሱት ስሞች የሚከተሉት ናቸው፤

አዝብጤ	ጫልቱ	ሐዳስ			
ጎንጤ	ለጄሳ	ለተሚካኤል			
አዛለች	ወርዶፋ	ሐጎስ			
እርገጤ	አያንቱ				
ጨቡዴ	መገርቱ		አርያም	እስፋ	ቀመሩ
ገብሬ	ቢራቱ				

እነዚህ ስሞች እዚህ እንዳደረግነው ተራ በተራ የተፃፉ አይደሉም፡፡ በነጠላ መስመር እየተለያዩ፥ ተሰበጣጥረው ነው ወደ ጎን የተፃፉት፡፡ ይህ የተደረገው የሕዝቦቹን አኗኗር ለመጠቆም መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ የስሞቹ ድርደራም በ"አዝብጤ" ጀምሮ በ"ሐጎስ" ማብቃቱ ምናልባት በነዚህ ስሞች በተለምዶ የሚጠሩት የጎሳ አባላት በአካባቢው መኖር የጀመሩበትን ጊዜ ለማመልከት የታሰበ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በነዚህ ሁለት ጎሳዎች አተያይና አስተሳሰብ ሌሎቹ እንደተቀነበቡ ለማመልከትም ታቅዶ ይሆናል፡፡ አንድ ወይም ሁለት የጎሳ ስም ብቻ ተጠቅሶ የሚገኘው ደግሞ፥ ያ ጎሳ በአካባቢው ከሚኖሩ ከሌሎቹ ጎሳዎች ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ቁጥር እንዳለው ለመጠቆም ይመስላል፡፡

የሚሠራውን የሥራ ዓይነት በመጥቀስም ቦታው የግብርና አካባቢ መሆኑ ከገበሬው የውሎ ተግባራት ጋር ተገልጿል፡፡ ማለዳ "ወገብ በመዛወር" የሚጀምረው አድካሚ የሥራ ቀን በምሽት "እንጨት ለቀማ" ይቋጠራል፡፡ ይህ ተደጋጋሚ፥ አድካሚና አሰልቺ የየዕለት ህይወት ነው፡፡ የሚያመርተው፥ የሚበላውና፥ የሚጠጣውም እንደዚሁ ተዘርዝሯል፡፡

በዚህ ተፈጥሮአዊ፥ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ አካባቢ ውስጥ ያለው ሕይወት ግን የረጋ ነው - ዝም ያለ የሚባል ዓይነት፡፡ የሚያጣድፈው ምንም ዓይነት ግፊት የሌለበት፥ "በርጋታ . . . በዝግታ . . ." የሚፈስ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በአዎንታዊ ስሜት የተገለፀ አይደለም፡፡ ቢያንስ በስላቅ፥ አለበለዚያም በአሉታዊ ስሜት የተሰነዘረ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ደራሲው፥ "በሌላ አገር የምትጣደፈው የምትፍለቀለቀው፥ የምትምቦለቦለው . . . ሕይወት. . . ." እዚህ በዝግታ በመፍሰሷ ማዘኑን ከገፅ 5-6 ባለው ገለፃ ውስጥ ባስተላለፈው ስሜትና፥ ከፍ ብለን ከጠቀስነው በመጀመሪያው አንቀፅ ውስጥ ከሚደጋገመው አዝማች መረዳት እንችላለን፡፡

ባለ 57 መስመሩና ባለ 385 ቃላቱ የአደፍርስ የመጀመሪያ አንቀፅ ልዩ ልዩ እሳቤዎችን ያዘሉ ቃላት በተለያየ መንገድ ተደርድረው የሚገኙበት ባለ ሁለት ገጽ አንቀፅ ነው፡፡ በነዚህ ቃላት መሀከል ያሉት አራት ነጥቦች ሰባት ብቻ ናቸው፡፡ ከነዚህ ሦስቱ በመጀመሪያዎቹ አራት መሥመሮች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በላይ፥ እነዚህን ቃላት ደጋግመን ተመልክተንና መርምረን የተረዳነውን አፍታትተን ባጭሩ ለማቅረብ ሞክረናል፡፡ ቃላቱን በዝርው ፍቻቸው ብቻ የሚመለከት አንባቢና ሀያሲ ሊስታቸው የሚችላቸውን ጉዳዮች መርምሮ ማግኘት የሚቻለው፥ ደራሲው በእነርሱ አማካይነት ሊያስተላልፍ፥ ሊጠቁም የፈለገው ስሜት (emotion) መኖር አለመኖሩን ከመጠየቅ በመነሳት ነው፡፡ ይህንን ዓይነቱ ጥያቄ እንዲጠየቅ የቃላቱ አሰዳደር እራሱ ካስገደደ ቆይቷል ማለት ይቻላል፡፡ የደራሲው አፃፃፍ ለአማርኛ ቋንቋ እንግዳ በመሆኑ ብቻ እንኳ ጥያቄዎች መጠየቅ ነበረባቸው፡፡ ቴክኒካዊ ፋይዳውን በይበልጥ ለመመርመርም ገና ወደፊት መጠየቅ ይኖርባቸው ይሆናል፡፡ ከዚህ ዓይነቱ

የጠይቅ-ጠይቅ ግፊት ተነስተን የሰነዘርናቸው ሃሳቦች ግን በደራሲው ብዕር በቀጥታ ያልተነገሩ፥ ዳኛቸው ወርቁ በአፃፃፍ ቴክኒክ ብቻ የተናገራቸው መሆናቸውን አጠንክሮ ማሳሰብ ያስፈልጋል። ለአማርኛ የልቦለድ አፃፃፍ ባህልም አንድ አዲስ ጥበባዊ አስተዋፅኦ መሆኑ ሊመዘገብ ይገባል።

ከዚህ ቀጥለን ለመመርመር የምንፈልገው በወ/ሮ አሰጋሽና በጭሰኛው፥ በሮማን እና በጎርፉ መሀከል የሚካሄዱትን ምልልሶች እና ቴክኒካዊ ፋይዳቸውን ነው።

ከፍ ብለን እንደተመለከትነው፥ አካባቢው "የእነበየዓይነቱ አገር" የሚባል ዓይነት ነው። ምድሩ፥ ሰዉ፥ እህሉ፥ ምግቡ በየዓይነቱ ነው። በጥቂት ቃላት፥ በቀላሉ የሚገለፅ ገር ባህርይ (character, feature, etc.) ያለው አካባቢ አይደለም። የአካባቢው ነዋሪም ሰብእና (personality) ገርኛ (simple) እና ቀጥተኛ (straightforward) አይመስልም። ውስብስብ (complex) ግን ይመስላል። በቀጥታና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ሃሳባቸውን ከመግለፅ ይልቅ፥ ብዙ ጊዜ፥ በተዘዋዋሪና በውስብስብ ስልት በተቀመረ ምሳሌያዊ ንግግር የሚናገሩት ወ/ሮ አሰጋሽም የዚህ አካላዊ አካባቢ (physical environment) ኅሊናዊ ምስሉ ሳይሆኑ አይቀሩም። በእርሳቸውና በጭሰኛው መሀከል በሚካሄደው ምልልስ ("ምልልስ" እንበለውና) ውስጥ በምሳሌያዊ ንግግር በሚጠቀሙበት ሁኔታና በአጠቃላይ የአነጋገር ስልታቸው በኩል፥ ደራሲው፥ በልቦለዱ የመጀመሪያ እንቀፅ ለሳለው ትርክምክም አካባቢ ኅሊናዊ አምሳያ አድርጎ ስሏቸዋል ማለት ይቻላል።

ድንገት ለሚመለከት፥ በአካባቢው ከሚገኙት ዋና ዋና ግዑዝ (physical) ነገሮችና ባህሎች በመጀመሪያው እንቀፅ ያልተዘረዘረ ያለ አይመስልም። ተከትሎት በሚመጣው በወ/ሮ አሰጋሽ ንግግርም ውስጥ የማይነሳ ነገር ያለ አይመስልም። ዘር ሊበደር ለመጣው ጭሰኛቸው ከመጣበት ጉዳይ ጋር ጠርሶ የማይገናኙ ጉዳዮችንና በሩቁ የሚገናኙ ጉዳዮችን እያነሱ ይተገትጉታል - ይነዘንዙታል። በእርሱ፥ በእርሳቸው እና በእርሳቸው ብጤዎች መሀከል ስላለው መሠረታዊ ግንኙነት በግድ ይነግሩታል። የእርሳቸውና የብጤዎቻቸው አጋር ስለሆነው እግዜርና ስለ ንጉሡ ነገስቱም ያላቸውን ሀሳብ በግድ ይግቱታል። ከዚህ በፊት በእርሱና በእርሳቸው መሀከል ተፈጥሮ የነበረውን፥ ያልጣማቸውን ጉዳይም ደጋግመው ያነሱበታል። ከእርሳቸው ንግግር የምንታዘበው አራምባና ቆቦ እየረገጡ ከዋናው ርእሰ-ነገር ጋር በቀጥታ ያልተገናኙ ምስቅልቅል ጉዳዮችን ሲያነሱ ሲጥሉ ነው። አነጋገራቸው እንደ አካባቢው ገባ-ወጣነት እና ዥጉርጉርነት ይመሰቃቀልብናል። በንግግራቸው ውጪያዊ መመሰቃቀል አማካይነት ደራሲው ሊፈነትው የፈለገው ዋናው ነገር ከፍ ብለን የገለፅነውን፥ የአካላዊውን አካባቢ ኅሊናዊ አምሳል በወ/ሮ አሰጋሽ አማካይነት መሳል ነው ብለን እናስባለን። ይህ የደራሲውን ጥበብ የምናስተውልበት አንድ ሌላ አዲስ ነጥብ ነው።

ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ የወ/ሮ አስጋሽን ንግግሮች ከእርሳቸው ግምባር፥ በእርሳቸው ዓይን፥ አጢነን የምናገኘው ነጥብ ነው። ይህ፥ በልቦለዱ ውስጥ ባላቸው ህይወት እንደማንኛውም ገፀባህርይ ካላቸው የመኖር ፍላጎት የሚመነጭ ነው። ስለዘር ብድር ብቻ፥ በቀጥተኛ ምልልስ፥ ከጭሰኛቸው ጋር መነጋገር፥ ለወ/ሮ አስጋሽ ፋይዳ ያለው ወግ አይደለም። ለእርሳቸው፥ ትልቁ ቁምነገር፥ በጢሰኛና በባላባት መሀከል እየላላ የመጣውን የሥልጣን ግንኙነት ማጥበቅ፥ የመደባቸውን የበላይነት ማጠናከርና፥ ከተቻለም ዘለዓለማዊ ማድረግ ነው። በዚህ ምክንያት ነው፥ በተለያየ መንገድ ርእዮተዓለማቸውን የሚጠቀጥቁት። አንባቢም ስለ እርሳቸው ገፀባህርይ (character) ከሁኔታው ብዙ ይረዳል።

ወ/ሮ አስጋሽ ነዝናዛ፥ ችኮ እና አሰልቺ ሆነው ነው የተሳሉት። ደራሲው ግን ይህንን ባህሪያቸውን አንድም ቦታ፥ ፊት ለፊት አይነግረንም። በአፃፃፍ ቴክኒኩ ግን ከአነጋገራቸው እንድንፈርድ ያደርጋል። ከዚህ በፊት በሌላ ፅሁፍ እንዳሰፈርኩት፥ ደራሲው የወ/ሮ አስጋሽን ሀሳበ-ደሀነት እና ንግግረ-መንቻካነት የሳለው ጥበባዊ በሆነ የምሳሌያዊ አነጋገሮች አጠቃቀም ነው። አንዳንዴ ሙሉ በሙሉ በሚጠቅሷቸው ምሳሌያዊ አነጋገሮች፥ በሌሎች ጊዜያት ደግሞ እየገመሱ፥ እየጎረዱ ባልታሰበ ጊዜና ሁኔታ በንግግራቸው ውስጥ በሚያስገቧቸው፥ ከ20 በሚበልጡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች አጠቃቀማቸው ስሏቸዋል። እንደ ታዋቂው ናይጀሪያዊ ደራሲ፥ እንደቺኑዋ አቼቤ (Fekade, 1982:1-14 እና 1985:24-27 ተመልከት)፥ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በመጠቀም፥ ሆነ ብሎ፥ የድርሰት አፃፃፍ ቴክኒኩን ለማበልፀግ የሞከረ የመጀመሪያው የሀገሪቱ ልቦለድ ደራሲ ዳኛቸው መሆኑም በዚሁ ፅሁፍ ተመልክቷል። ይህ ከወ/ሮ አስጋሽ አሳሳል የምናስተውለው ሦስተኛው ቴክኒክ-ነክ ነጥብ ነው ማለት ይቻላል (ፈቃደ፥ 1973)።

ባጭሩ፣ የወ/ሮ አስጋሽና የጭሰኛው ቆይታ የተቀረፀበት ምልልስ ከተለያየ ጠገግ (side or angle) ሲተነተን ልዩ ልዩ ስሜቶችን እና ሃሳቦችን እንዲያስተላልፍ በበሳል ቴክኒክ የተቀመረ ነው። እነዚህ ሦስት ነጥቦችም በአንባቢውና በሃያሲው ትክታዊ ንባብ የሚስተዋሉ እንጂ በድርሰቱ ውስጥ ፊት ለፊት የተነገሩ አይደሉም። ስለዚህም በቀጥታ ከመናገር ይልቅ በማሳየት ተቃኝቶ የሚፈስሰውን የዳኛቸውን የአፃፃፍ ስልት ይበልጥ እንድናስተውል ያደርጉናል።

ከሁለቱ ገፀባህርያት ምልልስ ያስተዋልነው ከአፃፃፍ ቴክኒኩ ጋር የተያያዘ ሌላ ነጥብ አለ። ይኸውም የምልልሱ ሚዛነቢስነት ነው። አንዱ ወገን ከመነጋገር ይልቅ መናገርን ስለሚያበዛ ውይይቱን ካንድ አቅጣጫ ብቻ እንዲፈስ አድርጎታል። ሚዛን ያጣ፥ የአንድ ወገን የራስወግ (monologue) ነው ብለን የምልልሱን ባሕርይ በአሉታዊ መንገድ ልንተች እንችላለን። ይህ ግን የደራሲውን የአፃፃፍ ክሂል በአሉታ መተቸት ተደርጎ መወሰድ አይገባውም። እንዲያውም የምልልሱ አወቃቀር

በእራሱ፣ ሚዛንቢስ ምልልስ÷ ልክ በህይወት እንደሚሆነው ሁሉ÷ በሥነፅሁፍም ውስጥ የሚከሰተው÷ አቻ ባልሆኑ ተወያዮች መሀል መሆኑን ስለሚፈነትው ደራሲው ሊደነቅ ይገባል። ምን ማለታችን እንደሆነ ጥቂት እናብራራ።

በወ/ሮ አሰጋሽና በጭሰኛው መሀከል ያለው ግንኙነት የበላይና የበታች ግንኙነት ነው። አሁን በምንወያይባቸው ገፆች ውስጥ ደግሞ የአበዳሪና የብድር ለማኝ ግንኙነት ነው ያላቸው። በዚህ ምክንያት አንደኛው ነፃ እና የልቡን ተናጋሪ÷ አባ ግድየለሽ ሲሆን÷ ሌላው ደግሞ ከሌላው የሚፈልገው ነገር ስላለው ነፃነት የሌለው÷ አንደበቱና አመሉ የተገታ ነው። ወ/ሮ አሰጋሽ ያሻቸውን በመናገር ይዝናናሉ እንጂ የሚያጡት ነገር የለም። ባለሃብትና ባለመብት ስለሆኑ እንዳሻቸው መራቀቅ ይችላሉ። ጭሰኛው ግን የሚፈልገውን የዘር ብድር ላለማጣት ሲል መብቱንና ነፃነቱን በገዛ አንደበቱ ይወስናል። ያለው አማራጭ÷ እውስጡ÷ አንጀቱን የሚያንገበግበውን ሁሉ ተናግሮ ነፃ ረሀብተኛ በመሆንና የአንጀቱን በአንጀቱ ይዞ÷ የተገኘችውን ብድር ወስዶ÷ ዘር ዘርቶ አምርቶ÷ አንገቱን እንደደፋና አንደበቱን እንደለጎመ በመኖር መሀል ነው። ከባድ ምርጫ ነው። የሚናገራቸውን አጫጭር ሀረጎች መመርመርና መረዳት ያለብን÷ ይህንን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ለመናገር አፉን በከፈተ ቁጥር እያቋረጡት ሀሳቡን አፉ ላይ አንጠልጥሎ የቀረበት ጊዜ የጀመረውን ዐረፍተነገር ከጨረሰበት ጊዜ በጣም ይበልጣል። ከገፅ 06 መጨረሻ እስከ 12 መጨረሻ ካለው ምልልስ ውስጥ የጭሰኛውን ባህርይ የምንገነዘበው÷ እርሱ ከሚናገረው ይልቅ እርሳቸው ሲናገሩት ለመመለስ ባለው ፍላጎትና÷ ይህንን ፍላጎቱን ለማሟላት ሞክሮ ሳይችል የቀረባቸው ሁኔታዎች እኛ ላይ በሚያሳድሩት ስሜት ነው። መታፈኑ በተደጋጋሚ ይሰማናል። ሃሳቡ እውስጡ ታምቆ መቅረቱ እያሳሰበን ነው ምልልሱ የሚያበቃ። ዳኛቸው÷ "ግፍ! በደል! ጭቆና" እያለ አያስተጋባም። ከእርሱ በፊት (እና በኋላም ማለት ይቻላል) በተጻፉት ልቦለዶች ውስጥ እንደሚደረገው÷ በፊት ለፊትና በግልፅ አጻጻፍ የጭሰኛውን መበደል በዝርዝር አይገልጽም። በመሀከላቸው ያሉትን ግንኙነቶች ግን ፊት ለፊት አጋጥሟቸው በግልፅ ሥሉ ያሳያል። ሥዕሉን ተመልክቶ÷ ምልልሱን አድምጦ÷ የግንኙነታቸውን ዓይነት መገምገምና አንድ አስተያየት ላይ የመድረሱ ሥራ ግን ለየንቁው አንባቢ እና ለየሀያሲው ተትቷል።

ከዚህ በላይ እንዳመለከትነው ጭሰኛው "አንደበተቢስ" ተደርጎ ነው የተሳለው። ለመናገር እየፈለገ ሳይችል ቀርቷል። ይህ <u>በአደፍርስ</u> ውስጥ ያለው ጭሰኛ የተሳለበት ቴክኒክ በ <u>እምቧ በሉ ሰዎች</u> ውስጥ ከተሳለው "አንደበተቢስ" ሕዝብ አሳሳል ጋር የሚነፃፀር ነው። <u>በአደፍርስ</u> ውስጥ የተጠቀመበትን ቴክኒክ ተመልክተናል። ከዚህ ቀጥለን <u>በእምቧ በሉ ሰዎች</u> ውስጥ የሀገሪቱን ህዝቦች አንደበተቢስነት ለየት ባለ ቴክኒክ እንዴት እንደሳለ እናሳያለን። ይህንን የምናደርገው÷ በቴክኒክ ብዙ ቁምነገሮችን መፈንተውን ሆን ብሎ የያዘ ደራሲ መሆኑን አጉልቶ ለማሳየት እንጂ ከያዝነው ነጥብ ለመራቅ አይደለም።

የሚጠቀምባቸው ቃላት ቀላል፥ ግልፅና ዘለለታዊ (daily, common-use words) ሆነው በአፃፃፍ ቴክኒኩ ግን ጥቅል ማኅበረሰባዊ ችግርን እንዴት እንደፈነተወባቸው፥ ግጥሙን ሙሉ በሙሉ ጠቅሰን ባጭሩ በመተንተን ሃሳባችንን ለማብራራት እንሞክራለን፡፡ ሁለቱም መጻሕፍት ውስጥ ዝምታ ያለውን ሚና አንባቢው እንዲያስተውል ይጠቆማል፡፡

ጥቅስ 02

እንደ መግቢያ

ሀሀሀ

ስትፏድድ
ስትባክን ውለህ

ትትት

ንፍሮህን ቃቅመህ
ዘባተሎህን ደርበህ፥

ችችች

አዛባና ሸንት
ከመሬት
የተኛህበትን አጎዛ
ዘልቆ ስታገኘው፥
ወገብህን ስትመቻች፥

ክክክ

ሾክ የወጋህን
ድንጋይ የመታህን
እየተመለካከትክ፥
ቅማልና ትኳን
የጋጠውን አካላትህን
እየደባበስክ፥

ይይይ

መልከኛውና ሻቃው
ጸሐፊውና ዳኛው
ማዶ ለማዶ ተፋጦ

ያሳደግኸውን
ሊቀማህ ሲተያይ፥

ኝኝኝ

በሆነ ባልሆነው
በየጊዜው
ስትጎተት፥ ስትታሰር
የምትመካበት ሕግ
ሲጠፋ
የምትለው አለኝ፥

ርርር

ሀብትህን ተገፈህ
መኖር አስጠልቶህ
ጦርህን ከጣራ
መኸርጠህ፥
ጫካ ቤቴ ብለህ
ስትዞር
ካገር አገር፥

ውውው

መንከራተት ሰልችቶህ
ሕይወት አንገፍግፎህ
መሬት መሬት
አስመልክቶህ፥
ሲስብህ
እናት አባትህ
የረገፉበት

አጽመ ርስትህ
ትዝታው፥
አፍ የሌለህ አንተ ዋቶ አደር
ሊሰማህ ይሆን-----ያ
ስትል የምስማህ
ያውቃል እዝጊያብሔር? (እምቧ በሉ ሰዎች፥ ሀ - ሐ)

"እንደ መግቢያ"፥ እምቧ በሉ ሰዎች ውስጥ 13ኛ ግጥም ሆኖ የቀረበ ነው ማለት ይቻላል። የተጻፈው የካቲት/1966 በመሆኑ በዘመን ከሌሎቹ ስብስቦች ይርቃል። የመጨረሻው ግጥም በ 1957 የተፃፈው "አይመረመሬ" ነው። በገፅ ቁጥር ከ 1-100 ገፅ በሚከታተሉት ከ 1945-1957 በተጻፉት ውስጥ አልተካተተም። የግጥሙ መጽሐፍ በታተመበት አካባቢ ከነበረው ለውጥ ጋር የተያያዘ "ለየት" ያለ ግጥም በመሆኑም ይሆናል፥ የርሱ የገፅ ቁጥር ከ "ሀ እስከ ሐ" የሚሄደው።

ይህ ግጥም ከሌሎቹ፥ በመድበሉ ውስጥ ካሉት ግጥሞች በይዘቱም ሆነ በቴክኒኩ የተለየ ነው። ይዘቱ ለብዙ ዘመናት የስቃይ ኑሮ የኖረውን ሕዝብ አበሳ ባጫጭሩ የሚገልፅና፥ ግጥሙ በተፃፈበት በየካቲት/1966 እየተጋጋለ የመጣው የለውጥ እንቅስቃሴ ይህንን ሁኔታ "ሊለውጥልህ ይሆን?" የሚል ብጤ ነው። ነገር ግን ለውጡን ከሕዝባዊ እንቅስቃሴ ጋር በቀጥታ አያይዞ የሚመለከት ሳይሆን የለውጡን ስሜት ከእግዜር ጋር አያይዞ የሚያጠይቅ ግጥም ነው። `ገጣሚው የደሀውን ሕዝብ ልዩ ልዩ የኑሮ ችግሮች በስምንት አንጓዎች ከገለፀ በኋላ በዘጠነኛው አንጓ እንዲህ ብሎ ግጥሙን ይደመድማል፣

አፍ የሌለህ አንተ ዋቶ አደር
ሊሰማህ ይሆን---ያ
ስትል የምስማህ
ያውቃል እግዚያብሔር? (ገፅ ሐ)

"እግዚአብሄር፥ የደሀውን ፀሎት ሰምቶ፣ ሁሌ ሲመርረው ወደ ፈጣሪው የሚያሳቅለውን ሕዝብ፣ አምላኩ አድምጦት ይሆን?" የሚል ጥያቄያዊ መደምደሚያ ነው። ይሁን እንጂ እንዲህ አይነቱ መደምደሚያ፥ ዞሮ ዞሮ፥ በጊዜው የነበረውን እንቅስቃሴ ከሃይማኖት አኳያ የመመልከትን አዝማሚያ መጠቆሙ አይቀርም። ነገር ግን ይህንን አተረጓጎም ወይም አስተያየት የገጣሚው ነው ለማለት በዚህ ግጥም ውስጥ ካለው መረጃ ይልቅ፥ ገጣሚው ደሀው ሕዝብ ሲናገር፥ ሲያሳቅል የሰማውን ተመርኩዞ ". . . 'እዝጊያብሔር ያውቃል?' ስትል የከረምከው አምላክ ሊሰማህ ይሆን?

ችግርህን ሊያውቅልህና ሊፈታልህ ይሆን?" ማለቱ ነው ለሚለው ያለው መረጃ ያመዝናል። መደምደሚያው አንጓ፥ የ 1966ን ለውጥ በችግረኛው ሕዝብ ዓይን ተመልክቶ፥ በርሱው እንደበት የተነገረውን አድምጦ፥ በራሱ አንደበት በጥያቄ መልክ ስለለውጡ ያለውን ሃሳብ የጠቆመበት ነው። ድምፀቱም (the tone) ለውጡን በሙሉ እምነት የሚቀበል ዓይነት ሳይሆን በጥርጣሬና በጥያቄ የሚመለከት ዓይነት ነው። ገጣሚው ሃሳቡን ገና አልወሰነም፥ በግልፅም አላወጀም። በዚህ ግጥም ውስጥ የሚታየው ሃሳብ ከ 1945-1957 ከተጻፉት ግጥሞች ጋር ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት በሌላ ጊዜ እንመለከት ይሆናል። ለጊዜው ስለአፃፃፍ ቴክኒኩ ባጭሩ እናወሳለን።

ግጥሙ ዘጠኝ አንጓዎች (stanzas) አሉት ማለት እንችላለን። እያንዳንዱ አንጓ አጭርም ይሁን ረዥም፥ በድምፀቀድ "ቃላት" ነው የሚጀምር። ከስምንቱ ሳድሳዊ፥ ስለዚህም ሀዘንተኛ፥ ድምፀቀዶች በኋላ የሚከተሉት የደሀውን ሕዝብ ኑሮ የሚገልፁ ስንኞች ናቸው። ሀሀሀ፥ ትትት፥ ችችች፥ ክክክ፥ ይይይ፥ ኝኝኝ፥ ርርር፥ ውውው* የሚሉት ድምፀቀዶች ችግረኛው ሕዝብ በየሆዱ ያመቀውን አበሳ የሚተነፍስባቸው ድምፆች ናቸው። በየዕለት ተዕለት ሕይወቱ፥ ብዙ ጊዜ፥ መከራውን አስቦና አፍታቶ በወጉ ከሚናገረው ይበልጥ በነዚህ ድምፀቀዶች አማካይነት የሚተነፍሰውን በዚህ ግጥም ውስጥ እንደ አዝማች እያመጣ የአፃፃፍ ቴክኒኩን አስልቶበታል። እርግጥ "አዝማች" የሚያሰኘው፥ ብዙ ጊዜ የአንድ ዓይነት ቃላትን ወይም ስንኞችን በአንድ የተወሰነ ምጣኔ እየደጋገሙ ማስገባት ሲታይ ነው ብሎ መከራከር ይቻላል። ነገር ግን በዚህኛውም ግጥም ቢሆን፥ የሚደጋገሙት ድምፆች ይለያዩ እንጂ እያንዳንዳቸው የታፈኑ ሃሳቦች መግለጫ "ትንፋሾች" በመሆናቸው አንድ ናቸው። ከየአንጓው ፊት የተወሰነ ምጣኔ ጠብቀውም ይደጋገማሉ። ስለዚህ "አዝማች" ናቸው ብንል አንሳሳትም።

ገጣሚው በዘጠነኛው አንጓ "አፍ የሌለህ አንተ" ያለውን፥ በትኩረት ስንመረምር ስለነዚህ አዝማቾች የምናስተውለው ሌላ ነጥብ አለ። አፍ የሌለው ሰው የማይናገር ማለት ነው። የማይናገር ሲባል ግን ስለ አካላዊ መሰናከል ወይም በቁሙ ድዳ ስለመሆን መናገር አይደለም። ገጣሚው ሀረጉን የተጠቀመበት፥ የሚነገር ብዙ ሃሳብ፥ ብዙ እውነት እያለ ተናግሮ ሃሳብን አለመግለፅን ለማመልከት ይመስላል። በነዚህ ድምፆች ("ትንፋሾች") ብቻ ነው የምትተነፍሰው ማለቱ ይመስላል። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም ከነዚህ ድምፆች በኋላ ገጣሚው የሚፅፋቸው ስንኞች "የአበሳ ትንፋሾቹን" በቃላት የሚፈቱ መስለው የሚታዩት።

* የሆሄዎቹ መጠን በግጥሙ ውስጥ ለአዝማቾቹ እንደተደረገው ሳይሆን ተስተካክሎ የተፃፈው የመስመሮቹን አረዳደፍ እንዳያዛባ ሲባል ነው። (አዘጋጆቹ)

ሌላው ነጥብ፥ ትትትን ተከትሎ ከሚመጣው አንጓ የመጨረሻ ስንኝ በቀር ሌሎቹን ትንፋሾች ወይም ድምፆች ተከትለው የሚመጡት አንጓዎች የመጨረሻ ስንኞች፥ ቤት የሚመቱት ቀድመዋቸው በመጡት ድምፆች መሆኑ ነው። በዚህ ዓይነት ቴክኒክ፥ አበሰኛው ሕዝብ በትንፋሹ የሚለውና ገጣሚው በቃላት የሚገልፀው ተሰናኝተው መገናኘታቸውን ማስተዋል ይቻላል። ቦታ ላለመፍጀት አጭሩንና የመጀመሪያውን አንጓ ብቻ ደግመን እንጠቅሳለን።

ሀሀሀ
ስትፈድድ
ስትባክን ውለህ (ገፅ "ሀ")

የብሶት ትንፋሽ የሆነው ሀሀሀ እና "ውለህ" ቤት የሚመቱት በ "ሀ" ነው። ሲፈድድ፥ ሲንፈቀቅ፥ ሲባዝን ሲደክም የቆየ ሰው ውሎውን እያሰላሰለ ከሚትከነከንባቸው ትንፋሾች አንዱ "እሀሀሀ . . ." ነው። ብሶተኛው፥ በገጣሚው አገላለፅ "አፍ የሌለው" ስለሆነ በትንፋሽ "ተናገረ" ቢባል ገጣሚው ደግሞ በስንኞቹ አማካይነት፥ በቃላት አፍታቶ ተናገረ ማለት ነው። ይህ ሃሳብ በተለይ በረዣዥሞቹ አንጓዎች ውስጥ ይበልጥ ግልጥ ሆኖ ስለሚታይ እነርሱን መመልከት ይጠቅማል።

ሌላው የቴክኒክ ጉዳይ፥ ድምፆች በፊደል የተቀረፁበትን ሁኔታ ይመለከታል። እነዚህ ድምፆች ወይም "የአበሳ ትንፋሾች"፥ የተፃፉት በተለያየ መጠን (size) ነው። መጠናቸው በትልቅ ጀምሮ እያነሰ ይሄዳል። ሀሀሀ ከሚለው ምሳሌ እንደምንመለከተው ሦስቱ የ "ሀ" መጠኖች የተለያዩ ናቸው። ይህ፥ ገጣሚው የትንፋሹን ብዛት (volume) እየቀነሰ መሄድ ለማመልከት ሆን ብሎ ያደረገው ነው ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ የግጥሙን መሠረታዊ ጭብጥ ይዞ የዋቶ አደሩ ብሶት ሊቀንስለት ይሆናል የሚለውን ሃሳብ ለመግለጥ የዋለ "ሥዕላዊ" ምልክት ነው ማለት ሳይቻል ይቀራል? በግጥሙ ውስጥ አንዴም ሳይለወጥ በየአበሳ ትንፋሾች አፃፃፍ ላይ፥ በተከታታይ፥ ባንድ ዓይነት መልክ መፃፉንና፥ ገጣሚው ስለሥነጥበብ ልዩ ልዩ ዘርፎች (ሥዕል፥ ሙዚቃ፥ ፎቶግራፍ፥ ፊልምና ሥነጽሁፍ) በድኅረ ምረቃ ትምህርቱ ያካበተውን እውቀት ተግምት ውስጥ አስገብተን ስንመለከት መላምታዊ ጥያቄያችንን ፍፁም መሠረተ ቢስ አድርጎ መቁጠሩ ያስቸግረናል።

የ<u>አደፍርስ</u>ን ጭሰኛም ሆነ የ<u>እምቧ በሉ ሰዎች</u>ን ዋቶ አደር የምንረዳቸው ከሚናገሩት ሳይሆን ከዝምታቸው ነው ማለት ይቻላል። ዳኛቸው ይህንን እውን ያደረገው ከዚህ በላይ በዝርዝር በተነተንነው የአጻጻፍ ስልቱ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ስለ"ሚዛነቢስ ምልልስ" ያስተዋልነውን በማቅረብ ወደጀመርነው ውይይታችን እንመለስና በ<u>አደፍርስ</u> 16 ገፆች ውስጥ ስለቀረበ ሌላ የምልልስ ዓይነት ያለንን አስተውሎትና ግኝት እናቀርባለን።

ከወ/ሮ አሰጋሽና ከጭሰኛው ምልልስ በኋላ የአካባቢው አትሞስፌር ይለወጣል። የከብቶቹ የሥምሪት ሰዓት በሕይወት ሲንቀለቀል፥ አካባቢው ሁሉ በእንቅስቃሴና በጥድፊያ ላይ እንዳለ ሆኖ ይገለፃል። ከብቶች ወደየቤታቸው እያመሩ ነው። እንቅስቃሴያቸው በዝምታ የሚከናወን አይደለም። በልዩ ልዩ ድምፆች የታጀበ ነው።

ጥቅስ 03

የፊንጣው ሲርሲርታ፥ የዝንቡ ዝዝታ፥ የንቦቹ እምምታ፥ በዙሪያ ጉብታው ያስተጋባል። አውራ ዶሮ አልፎ አልፎ ይኮኩላል። እውሃ መቅጃው ኩሬ የእንቁራሪቶች ሠርግና ምላሽ ሆኗል። ላሞች ያምቡዋሉ፥ ጥጆች ያስተጋባሉ፥ ያምባርቃሉ፣ ያ ጭር ብሎ የሚውለው ቀዬ ላንዳፍታ በሕይወት መምቦልቦል ይጀምራል (አደፍርስ 12-13)።

በዚህ የተጣደፈ እንቅስቃሴ ውስጥ በጎርፉና በሮማን መሀከል የሚካሄደውም ምልልስ በወ/ሮ አሰጋሽና በጭሰኞቻቸው መሀከል እንደተካሄደው ምልልስ ያንድ ወገን የበላይነት የተጫነው አይደለም።

ጥቅስ 04

"ሮማን--
"ማነህ አንተ?" ድንግጥ ብላ የሽምጡን አጥር ተገን በመያዝ።
"ሮማን አይዞሽ እኔ ነኝ--
"ማ--
"እኔ--
"ማ አብዬ--" ድንጋጤዋ በረድ ባለ መንፈስ።
"የለም፣ ጎርፉ ነኝ-- ዋንዛ ይገፎልሻለሁ ---
"እኔ ዋንዛ አልፈልግም ---
"ቅሞም ብትፈልጊ አለኝ --
"የለም አልፈልግም --
"ኮሽምስ?
"አልፈልግም! ደግሞ ያልገባኝ አይምሰልህ የመጣህበት --
"ኮክስ?
"አትቀልድ እባክህ...
"ቀጋስ፥ ሎሚስ?
"አልፈልግም አልኩህ እንግዲህ --
"እውነትሽን ነው አሁን?
"እንዴታ! እውነቴን ነው ... (አደፍርስ፥ 1962፥ 13)

የሮማንና የጎርፉ ምልልስ አጫጭርና እንደመቸቱ የተጣደፈ ነው። እሚፈለገው ነጥብ ላይ ለመድረስ የሚቻኮል ዓይነት ነው። በአጫጭር ጥያቄና መልስ ሃሳባቸውን በእኩልነት ይለዋወጣሉ። የበላይነትና የበታችነት ስሜት በነርሱ ዲያሎግ ውስጥ አይታይም። እነርሱም ዲያሎጋቸውም አቻዊነትን እና ሚዛናዊነትን ይጠቁማሉ ማለት ይቻላል። ጎርፉ ዊወኔን አግኝቶ ለማነጋገር ያለው ፍላጎት ከሮማን ጋር ያወያየዋል። በመጀመሪያ ላይ ሊያባብላት ቢሞክርም እንቢተኛነቷ ጎልቶ ይወጣል። ቀስ እያለ ግን የእርሱንና የእርሷን ፍላጎት እያቀራረበ ሲሄድ ፍላጎቷን ለማሟላት ስትል የእርሱን ጥያቄ ወደ ማሟላት መንፈሷ ማዘንበል ይጀምራል። በፈጣን ሂደቱ፥ ከሃሳብ ልዩነት ተነስቶ ባጭር ጊዜ ውስጥ የስሜት ሚዛናዊነትን በተወያይዎቹ መሀል ፈጥሮ ወደ መግባባት አዘንብሎ የሚያልቅ የአቻዎች ምልልስ ነው።

ዳኛቸው ወርቁ ራስወግ (monologue) ሊባል ከሚችለው የወ/ሮ አሰጋሽና የጭሰኛው ምልልስ ወደ አጫጭር ዲያሎግ ባደረገው ፈጣን ሽግግር ሰዎች በማህበረሰብ ውስጥ ባላቸው ቦታ አነጋገራቸው እንደሚወሰን አሳይቷል ማለት ይቻላል። በጭሰኛቸው ላይ ያላቸው የኢኮኖሚ ሀይል ወ/ሮ አሰጋሽን ለረዥም ደቂቃዎች እንደልብ ሲያናግራቸው ታይቷል። ዘር ተበዳሪውም ንግግራቸው ባይጥመውም እንዲሰማቸው መገደዱ በግልፅ ተስሏል። የማዳመጥ ችሎታውና ግዴታውም የሚመነጨው ለሄደበት ጉዳይ አዎንታዊ መልስ ለማግኘት ካለው ፅኑ ፍላጎት ነው። በሮማንና በጎርፉ ምልልስ ውስጥ ግን ራስወግ ቦታ የለውም። እርግጥ፥ ጎርፉ የሚፈልገውን ርእስ ወደ ምልልሱ ለማምጣት ተፅዕኖ ያደርጋል። በተረፈ ግን አቻዊ፥ ተውኔታዊ፥ ህይወታዊና የሚያጓጓ ምልልስ ነው። በሁለቱ ምልልሶች፥ ደራሲው የተለያዩ ቴክኒኮችን በመጠቀም ረቀቅ ያለ ሃሳብ አስተላልፏል ማለት ይቻላል።

ማስታወሻዎች

1. የዚህ መጣጥፍ የመጀመሪያ ማስታወሻዎች የተጫሩት በ1973 ነው። ስለ አማርኛ ልቦለድ የሚሰጡትን ሁለት ኮርሶች ሳስተምር እክፍል ውስጥ እገለገልባቸው ከነበሩት ማስታወሻዎች ከአደፍርስ የመጀመሪያ ምዕራፍ ጋር የተገናኙትን አጠናቅሬ፥ የመጀመሪያውን ረቂቅ፥ በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ለተዘጋጀው ለ "ሁለተኛው የተለያየ ርዕሳነ ይዘቶች ሴሚናር (Multi-Disciplinary Seminar)" ነሐሴ/1987 አቅርቤያለሁ። ለኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት የመጀመሪያ በይነ-ሙያዊ ሴሚናርም ግንቦት 1990 አሻሽዬ አቅርቤው ነበር።

2. የልቦለድ ኮርሶችን ሳስተምር አንድ ያስተዋልኩት ፕሮብሌም አለ። ፕሮብሌሙ ከማስተማሪያ ፅሁፍ ጋር የተያያዘ ነው። አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ የተዘጋጀ ውስጥ ከተሰነዘሩት መነሻ ሃሳቦች እና፥ በጋዜጣና በመፅሄት በወጡ አንዳንድ ታዋቂ ፅሁፎች ውስጥ ከተነገሩ አንዳንድ ነጥቦች በቀር ስለ አማርኛ ልቦለዶች የተደረጉ ትንተናዎች አልነበሩም ማለት ይቻላል። በዚህ የተነሳ፥ መምህሩ፥ ባንድ በኩል፥ ከብርሃንና ሰላም ጋዜጣ እንስቶ እስከ 1966 በወጡት ልዩልዩ ጋዜጦችና መጽሔቶች ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ ስነጽሁፍ የተባለውን ማደን ይጀምራል። በሌላ በኩል፥ በየዕለቱ ለሚያከናውነው ትውር ቀመስ ትምህርት የራሱን የቅርፅና የይዘት ትንተና በምሳሌነት እያቀረበ ተማሪዎቹን ያስተምራል። ስለ ልዩ ልዩ ልቦለዶች የሚናገረውን አብሳልቶ ለመፃፍ ከጊዜ ጋር ሲታገል የራሱ ተማሪዎች የእርሱን ሃሳብ፥ በገባቸው መልክ፥ በዲማፃቸው ውስጥ አስፍረውት፥ በጋዜጣና በሬዲዮም ብኩርናውን ሳይጠቅሱ አስተላልፈውት ይገኛል። አሁን እርሱ መጣጥፍ ሊፅፍ ሲያስብ ወደ ተማሪዎቹ ዲማፅም እንዲሄድ የምርምር ደንብ ግድ ይለዋል። ፕሮብሌሙን በዚህ መልክ ለጊዜው ማንሳት ያስፈልጋል በሚል ነው ይህ ማስታወሻ መጫሩ።

3. እዚህ ላይ አንድ የግል አስተያየት መሰንዘር ይፈቀድልኝ። አቶ ተክሉ ሚናስ የአቶ ዳኛቸው ወርቁ የሥራ ባልደረባና ወዳጅ እንደነበሩ ይታወቃል። ስለዚህም ስለደራሲው ስራዎችና ስለ ሕይወት አመለካከቱ ለማወቅ ከሌሎች ተመራማሪዎች የተሻለ ዕድል ነበራቸው ብዬ እገምታለሁ። ደራሲው (አቶ ዳኛቸው) በህይወት በነበሩበት ጊዜ አቶ ተክሉ በፃፉት የኤም.ኤ ዲማፅ ውስጥ ይህንን አጋጣሚ በወጉ እንደተጠቀሙበት የሚጠቁመኝ በቂ ሃሳብ አለማግኘቴ ዲማፁን ሳነብ አትከንክኖኛል። ይህንን የምለው፥ ከደራሲው ሊገኙ የሚችሉ፥ በደራሲው የፈጠራ ስራዎች ላይ ለሚደረጉ ምርምሮች የሚጠቅሙ ተጨማሪ መረጃዎች ዛሬ ሊገኙ አይችሉ ይሆናል ከሚል ሀዘን ተነስቼ ነው። ወይስ አቶ ተክሉ አንድ ቀን የሚነግሩን ነገር ይኖር ይሆን? በተስፋ እጠባበቃለሁ !!!

4. ይህ መጣጥፍ ጥቂት ተስተካክሎ ከመታተሙ በፊት "ትውፊት" ለተባለ ሴሚናር በ 1973 ቀርቦ ነበር። ጥቅሱን በስቴንስል ተባዝቶ በተሰራጨው ፅሁፍ ውስጥ፥ ገፅ 09 ላይ መመልከትና ማነፃፀር ይቻላል። በተጨማሪም፥ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ መፅሔት፥ ቁ. 3፥ 1985፥ ገፅ 13 ይመልከቱ።

ጥቅስማ (Reference)
(ስራዎቹ በታተሙበት ቅደም ተከተል የተዘጋጀ)

ዳኛቸው ወርቁ፥ አደፍርስ፥ ንግድ ማተማያ ቤት፥ 1962፥ 330 ገፅ፤ (መታሰቢያነቱ ለልዑል ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል፥ ለራስ አርአያ (የአፄ ዮሐንስ አጎት)፥ ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ፥ ለደጃዝማች ባልቻ ሣፎ፥ እና ለራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው)።

ብርሃኑ ዘሪሁን፥ "አዲሱ መፅሀፍ አደፍርስ" መነን፥ ግንቦት 21/1962፤ እና ፈቃደ (ጥቅምት 1985)፤ "የስነፅሁፍ ሂስ ምንጭ (መድበል ፬3፥ 1962-1966)"፥ (ያልታተመ) ገፅ 33-35።

Daniachew Worku. *The Thirteenth Sun*. Heinemann, African Writers Series, No. 125, 1973, 170 pages. (Dedicated to Tewodros Gebre-Amlak.)

Sahle Sellassie Berhane Mariam. ''The Novels of Daniachew Wroku,'' *The Ethiopian Herald,* October 27, 1974. Also see Fekade Azeze (October 1992), "Articles on Ethiopian Literature - a Sourcebook: 1949-1974" (Unpublished), pp.313-317.

Kane, Thomas Leiper. 1975. *Ethiopian Literature in Amharic*. Weisbaden: Otto Harrassowitz.

ዳኛቸው ወርቁ፥ እምቧ በሉ ሰዎች (ግጥሞች) ፥ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፥ 1967፥ ማውጫ፥ እንደ መግቢያ፥ 100 ገፅ (መታሰቢያነቱ ለደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት)።

ታሪክነህ አጥናፉ፥ "የዳኛቸው ወርቁ የአጻጻፍ ስልት፥ በአደፍርስ"፥ 1970፥ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል የቀረበ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ (ካሁን በኋላ ዲማፅ)።

ንብረት ምስክር፥"አደፍርስ የቋንቋው ይዞታው"፥ 1971፥ ዲማፅ።

ታምራት ተስፋዬ፥ "የዳኛቸው ወርቁ አደፍርስ (ገፀ ባህርይ) ትንተና"፥ 1972፥ ዲማፅ፥ 49 ገፅ።

Molvaer, Reidulf Knut. 1980. *Tradition and change in Ethiopia: social and cultural life as reflected in Amharic fictional literature,ca.1930-1974*. Leiden: E.J. Brill.

ፈቃደ አዘዘ፥ "ትውፊት በሥነፅሁፍ ውስጥ"፥ <u>የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የስነፅሁፍ መፅሔት</u>፥ ቁ. 6፥ 1985፥ ገፅ 1-19። (ይህ ፅሁፍ፥ ከመታተሙ በፊት ትውፊት በሚል ርእስ ከሐምሌ 1-2/1973 ለተካሄደው ሴሚናር ቀርቦ ነበር።)

ዘውዴ አክሊሉ፥"በ<u>አደፍርስ</u> ውስጥ የሚገኙ ምሳሌያዊ አነጋገሮች"፥ 1973፥ ዲማፅ፥ 43 ገፅ።

Assefa Aregahegne. "The origin and development of Amharic literature." AAU, School of Graduate Studies. M.A. Thesis. 1981. 123 pp. Unpublished.

Fekade Azeze. "Folklore in Literature: Some Aspects of Achebe's Use of Proverbs in *Things Fall Apart* and *Arrow of God,*" in *Studies and Documents*, No. 3, 1982:1-14. (A Bi-lingual journal published by EACROTANAL, Zanzibar, Tanzania.)

Teklu Minas. "Daniachew Worku's writings: Three Plays and Two Novels." AAU. School of Graduate Studies. M.A.Thesis. 1983. 64p. Unpublished.

Fiqre Tolosa. 1983. "Realism and Amharic literature (1908-1981)." PhD. Dissertation, University of Bremen.

ሽባባው ወሌ፥ "የገፀባህሪ ግጭትና ጭብጥ ትንተና በ<u>አደፍርስ</u>ና <u>ከአድማስ ባሻገር</u>"፥ 1976፥ ዲማፅ 56 ገፅ።

ዳኛቸው ወርቁ፥ <u>የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ</u>፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፥ የንግድ ማተሚያ ቤት፥ የመጀመሪያ እትም 1977፥ ማውጫ፥ መቅድም፥ 7-10 ገፅ፤ መግቢያ 11-18 ገፅ፤ 21-400፥ ቃላት 401-407።

ትንሳኤ ብርሃኔ፥ "የሥነቃል አጠቃቀም በ<u>አደፍርስ</u>ና በ<u>ፍቅር እስከ መቃብር</u>"፥ 1978፥ ዲማፅ፥ 95 ገፅ።

ማርታ ባዴ፥ "ገለፃ በአምስት ዐበይት የአማርኛ ልቦለድ ደራስያን ሥራዎች ውስጥ"፥ 1978፥ ዲማፅ፥ 71 ገፅ።

መሀመድ አሊ፥ "ግነት በሀዲስ ዓለማየሁ፥ በዳኛቸው ወርቁና በበዓሉ ግርማ ልቦለዶች"፥ 1978፥ ዲግፅ፥ 74 ገፅ።

ተንሳይ ይገዙ፥ "የፊውዳል ወይዛዝርት በአራት ደራስያን ልቦለድ መፃህፍት ውስጥ"፥ 1978፥ ዲግፅ፥ 66 ገፅ።

መስፍን አባተ፥ "ማኅበራዊ ልማድ በፍቅር እስከ መቃብርና አደፍርስ ልብወለድ መፅሐፍት ውስጥ"፥ 1978፥ ዲግፅ፥ 41 ገፅ።

ሞሴ ፋንታ፥ "ሃይማኖት በ <u>ፍቅር እስከ መቃብር</u> እና በ<u>አደፍርስ</u>" 1978፥ ዲግፅ፥ 48 ገፅ።

ዳኛቸው ወርቁ እና አምሳሉ አክሊሉ ፥ <u>የአማርኛ ፈሊጦች</u>፥ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፥ ንግድ ማተሚያ ቤት፥ የመጀመሪያ እትም 1979፥ 296 ገፅ፥ መግቢያ 3-6 ገፅ ።

መኮንን ምንዳ፥ "የፎክሎር አጠቃቀም በዳኛቸውና በሣህለ ሥላሴ የእንግሊዝኛ ልቦለድ ውስጥ"፥ 1979፥ የውጭ ቋንቋዎች ክፍል፥ ዲግፅ፥ 83 ገፅ።

ቴዎድሮስ ካብታሙ፥ "ልብ ሰቀላ በአራት የአማርኛ ረጅም ልቦለድ ደራስያን ሥራዎች ውስጥ"፥ 1981፥ ዲግፅ፥ 79 ገፅ።

ታጠቅ ታደለ፥ "ቅናት ከ1962--1980 ድረስ በወጡ የአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ"፥ 1981፥ ዲግፅ፥ 57 ገፅ።

ይልማ ደምሰው፥ "የጉዱ ካሣ፥ የአደፍርስና የካሳሁን ማኅበራዊ ዕይታ"፥ 1986፥ ዲግፅ፥ 70 ገፅ።